# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 5 ቁጥር 5 ጥቅምት 28 ቀን 2014 ዓ.ም.

## ኢትዮጵያችን እንድታሸንፍ ዘረኝነት ይቀበር

ሀገራችን ምድር ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመቃኘት ኢዮጵያችን አንደ ሀገር የመቀጠል ሁኔታዋ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል ቢባል ማጋነን አይደለም። "እኛ ያልገዛናት ኢትዮጵያ ትበታተናለች" ያለን ወያኔ/ህወሓት በአንድ በኩል፣ "ፊንፊኔ ኬኛ" ባዩ ኦነግና ኦነግ ሸኔ በሌላ በኩል ከከፈቱት ጣምራ ጦርነት በተጨማሪ "ለኦሮሚያ የምትስማማዋን ኢትዮጵያን እንፈጥራለን" ባዩ የመንግሥት አካል ቅዠት ተደማምረው እውን ኢትዮጵያ ፈራርሳ "ተረት ተረት" እንዳትሆን ያለንን ስጋት እናጋራለን። ኢትይዮጵያችን ላይ ያለ የሌለ ኃይላቸውን ይዘው የተነሱባትን የህወሓት ሀገር አጥፊዎች፣ የተባባሪዎቻቸውን የውጭ መንግስታት የወያኔ ማሚቶነት ስንቃኝ ምንጊዜም ለሀገራችን ቀና የማያስቡት ባህዳን ኃይሎች እኛ እናጨበጭብላቸዋለን እንጂ እነሱ ጥንትም አጥፍተውናል ዛሬም መዳከማችንን፣ መድቀቃችንን መበታተናችንን ፈላጊዎች ነበሩ ናቸውና አንድነቱ ቢኖረን እኛው ለእኛው እንደምንበቃ ባሳየናቸው ነበር።

የዛሬ ሦስት ዓመት ተኩል "ለውጥ" በኢትዮጵያ ተብሎ የወያኔ አመራር ወደ መቀሌ እንዲመሽጉ ሲደረግ በሀገሪቷ ላይ ለ27 ዓመት የሰነቀሩትን መርዘኛ የዘር ሕገ መንግሥት ይዞ የትም እንደማይደረስ ደጋግመን ጠቁመን ነበር፤ አሁንም እንደግመዋለን። ***<u>የአሁኑ ጦርነት ቁልፉ የወያኔ የዘርና ቋንቋ አከላለል ብሎም ሕገ መንግሥቱ ነው።</u>*** ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሬ ተነካች ብሎ ቀፎው እንደተነካ ንብ ዘርና ሃይማኖት ሳይገድበው መንቀሳቀስ የሚያሳየን ሕዝባችን አሁንም ለሀገሩ ሟች፣ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜቱን ፈላጊ፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማውን አክባሪ መሆኑን ነው። ይህንን የዘር አስተሳሰብ በጥሶ ኢትዮጵያዬ እያለ የሚተምን ሕዝብ፣ አሁንም በአጥንትና በደሙ ሀገሩን ሊያድን የተነሳሳ ትውልድን ነው በዘርና ቋንቋ ለማሰር የሚፈለገው። አዎን! አሁን ፊታችን የተደቀነው ቅድሚያ በወያኔ/ህወሓት የተከፈተብን ወረራ መመከት ብቻ ሳይሆን ወያኔ/ህወሓትን መቅበር ነው። ይህንን ጦርነት በድል ለመወጣት ሀገራችን የተዋጊ ችግር እንደሌለባት በሚያስደንቅ መልኩ ሕዝባችን እያሳየ ያለው መነሳሳት ምስክር ነው። ይህ ጦርነት በመንግሥት ድል አድራጊነት መጠናቀቁን የምንሻው በመንግሥት በኩል የሚደረገው የኢትዮጵያ ሀገራችንና የሕዝባችን ቀጣይ ሂደት የሰመረ ነው ከሚል ቅዠት ሳይሆን ያለ አግባብ እየረገፉ፣ እየተጨፈጨፉ ከአሉ ምስኪን ወገኖቻችን አንጻር፣ በዋነኛነት ደግሞ ኢትዮጵያችን ከነችግሯ እንድትኖርልን ስለምንመኝ ነው። ኢትዮጵያችን ከምትፈራርስ እኛ ተርበን መሰቃየቱን እንመርጣለንና። ኢትዮጵያችን ከምትበታተን ለአምባገነኖች ተንበርክከን አንድነቷን እንፈልጋለንና። ኢትዮጵያችን ተረት ተረት ከምትሆንብን ጭቆና፣ ብዝበዛ፣ እስር፣ እንግልት፣ ስደትን መቀበል ይሻለናልና። ይህ ነው ኢትዮጵያዊነት ስሜት፣ ይህ ነው ኢትዮጵያዊነት አኩሪ ባህል። ለኢትዮጵያዊነት የተሰደዱት፣ በእሥር ያሉ፣ የተራቡት፣ ጡጧቸውን በግፍ የተነጠቁት ሕጻናት፣ ምርኩዝ የያዙት አዛውንት፣ የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ወገኖች፣ ሌሎች ሌሎች ለሀገር ሲሉ መከራን ተሸክመዋል አሁንም ይሸከማሉ፣

ኢትዮጵያችን ከሁሉም በላይ ናትና። ይህም ነው የአገዛዞች መከራ ቢፈራረቅብንም ሀገር እልውናዋ ሲናጋ ገዳይና አምባገነን ለሆነው መንግሥት ሳይቀር አለንልህ የምንለው። በዐድዋ ምንሊክ ተከተለኝ ሲሉ ችግሩን አራግፎ የገሰገሰላቸው ሕዝብ ኢትዮጵያችን የአፍሪካ ኩራት ሁና ከድሉ ጫፍ እንድትቀመጥ አድርጓታል። የሱማሌን ወረራ በድል የመወጣት ታሪክ የነበሩ ስህተቶች እንደተጠበቁ ግድያና እስሩን ከቁብ ያልቆጠረ ትውልድ ውጤት ነበር። የሻቢያና ወያኔ ባድመ ጦርነት ድል ወያኔ/ህወሓትን ከመደገፍ ሳይሆን ሀገሬን ያለ ጀግና ደምና አጥንት ውጤት ነው። ዛሬም የዶር ዐብይ አሕመድ ዱባ ዱባ ስህተቶች እንደተጠበቁ ኢትዮጵያችን ያለ ትውልድ አጥንቱን ሊከሰክስ ደሙን ሊያፈስ ሲነሳ የምንደግፈው ኢትዮጵያችን እንዳትፈርስብን ዛሬም ኢትዮጵያችን ብለን ነው።

ይህ ጦርነት ዛሬ እደረሰበት ደረጃ ይደርስ ዘንድ የህወሓት ጥንካሬ ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ደካማ አመራር ጭምር መሆኑን የምንናገረው ከአለፉት ሦስት ዓመት ተኩል ተመክሮ በመነሳት ነው። እንደ መንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ የዶር ዐብይ አሕመድን ያህል ድጋፍ የተቸረው መሪ አልነበረም ቢባል ማጋነን አይደለም። ግና ይህንን ሕዝባዊ ድጋፍ ተጠቅመው ኢትዮጵያዊነትን ከማውራት ይልቅ ሊገነቡ አልቻሉም። ኢትዮጵያዊነትን መገንባት ማለት ወያኔ/ህወሓት ቀርጎፎ ያሰረበትን የዘረኛ ሕገ መንግሥት መበጣተስ ነበር፤ አላደረጉትም። የወያኔን ሕገ መንግሥትና የዘርና ቋንቋ አከላለል ይጊቼ ኦሮሙማን ማዕከል ያደረገ ብልጽግና ብቸኛ የመደመር ፍልስፍና እንደሆነ የሄዱበት አካሄድ ሀገሪቷ ዛሬ ለደረሰችበት አሳዛኝ ሁኔታ አብቅቷታል።

በትንሹ ለማስታወስ ያህል ዶር ዐብይ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት በበቁ ወራት አዲስ አበባን በፍጥነት ለመውረር በለገጣፎና ቡራዮ አካባቢ የተንቀሳቀሰውን የኦነግ ኃይል አላየሁም አልሰማውም ብሎ ከማለፍ ባሻገር ወረራውን ገትረው የተከላከሉትን የአዲስ አበባ ወጣቶች በየእሥር ቤቱ መታጎር የሚዘነጋ አይደለም። በጊዜው ይህን ጉዳይ ለማስቆም ኢትዮጵያዊነቱን የፈለገውን ሕዝብ ተገን አድርገው ያለማቅማማት ሕገ መንግስቱ ላይ ያነጣጠረ እርምጃ ወስደው ቢሆን የዘርና ቋንቋን ክልል ንደው ሁኔታዎችን ቀይረው ዘረኞችን አንገት ባስደፉ ነበር፤ አልሆነም። የዚህ በዝምታ መታለፍ የሻሸመኔን እልቂትና ውድመት ሲያስከትል የተደረገው የሙታን ዘር ቆጠራ እየገሰገሰ በጋምቤላ እና ቤኒ ሻንጉል መተከል አካባቢ እስከዛሬ ያላባራ የአማራ እልቂትን ሲያስተናግድ መንግሥት ምን የመከላከል እርምጃ ወሰደ ብንል አይቶ እንዳላየ ማለፍ ነበር። ሁኔታዎች ለዘረኞችና ለአጥፊዎች እየተመቻቹ አጣዬ ሙሉ በሙሉ መውደሟ አይዘህ ባዩን የተማመነ አሸባሪ የሚጨፈጭፈው አማራን ነውና አድማሱን አስፍቶ በወሎ ደሴንና ኮምቦልቻን ደም ጠጥቶ ንብረት አውድሞ ዛሬ አለንበት የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሰናል። እስክንድር ነጋ በአዲስ አበባ የኦሮሚያ ይገባኛል ጉዳይ ለተዘረጋው መሰሪ ተግባር ተጋፍጦ "ባልደራስን" ሲመሠርት አፋጥኝ ምላሽ በመስጠት "ጦርነት አውጃለሁ" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ እንዳሉትም እስክንድርና አጋሮቹን በእስር ሲያሰቃዩ ምነዋ ለአሸባሪው ኦነግ ሸኔ ሆዳቸውን ባር ባር አላቸው ቢባል "ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት" ይሆንብናል ጉዳዩ።

## *<u>የሰሞኑ የክተት ዘመቻና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፦</u>*

እውን ኢትዮጵያውያን በራሳችን አይደለም የውጭ/ባህድ ወራሪ ያልፈጸመውን ግፍ ህወሓት በአንድ በኩል ኦነግ ሸኔ በሌላ በኩል በተለይ ሳይሆን በትክክለኛነት አማራውን እየጨፈጨፉ ነው። ዱቄት የሆነው ህወሓት በነፋስ ተገዞ ከመቅጽፈት ወሎ ሲገሰግስና ጦርነቱ በረቀቀ ዘዴ አማራ ክልል ላይ አማራን ሲያጭድ እየተመለከትን ነው። "ዛሬ ዘመኑ የቴክኖሎጂ ነው፣ ጊዜው ያለፈበት የውጊያ ስልት አይሠራም" ተብሎ ሕዝብ እንዲዘናጋ ተደረርጎ አሸባሪው ህወሓት፤ መንግሥትና ሻቢያን ከትግራይ

አስወጥቶ ወሎ ሲገሰግስ እውነትም ዱቄት መሆኑ በነፋስ እገዛ ይምዘገዘግ ዘንድ እረድቶታል ልንል እንገደዳለን። ጦርነቱ ዛሬ ሰሜን ሸዋ ዘልቆ ከሚሴ ደርሷል። ይህ ጦርነት በቀጣይነት አዲስ አበባ ዘልቆ ከተማዋ የዕልቂት መዲና ሆና ኦነግ ከተማዋን ይቆጣጠራል? ወይስ ጠቅላይ ሚንስትሩ ከኦነግ ተደራድረው የህወሓትን ዳግም ማንሰራራት ድባቅ ይመቱታል? እንደፖለቲከኛ የሚታዩ ትንታኔዎች ናቸው። መንግሥት አሁን በአለበት ሁኔታ ጦርነቱ እንደከበደው ከሚጠቁሙ ሁኔታዎች የሰሞኑ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምስክር ነው። አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መንግሥት አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ ከመደበኛው ሕግ ውጪ ስልጣን ለሌሎች በመስጠት የሚጠቀምበት ማስታገሻ መርፌ ነው። መለስ ዜናዊ በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ሲሸነፍ ሽንፈቱን ለመቀልበስ ያደረገው ዓይነት እንደምሳሌ ይጠቀሳል። እውነት ለመናገር የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ መንግሥት እዚህ አዋጅ ማውጣት ድረስ ሳይደርሱ፣ ህወሓትም እዚያው በትግራይ ተቀብሮ በቀረ ነበር ግና የወያኔ/ህወሓት የ27 ዓመት የረቀቀ ተንኮል ያለማገናዘብ ውጤት ዛሬ ዱቄቱ ወያኔ ሀገርና ሕዝብ ዱቄት እያደረገ ይገኛል።

እውነት ለመናገር ወያኔ/ህወሓት እንኳን ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ትግራይ የሚገባው ቡድን አይደለም። ጠቅላይ ሚንስትር ዶር ዐብይ እንዳሉት እንጥቀስላቸውና ቦታው መቃብርና መቀበር ብቻ ነው። መንግሥት እራሱ አሸባሪ ብሎ የሰየመው የህወሓት ቡድን መደምሰስ ሲገባው በአለፉት ቀናት ደግሞ “የያዘውን አካባቢ ለቆ ትጥቁን ከአወረደ ለድርድር ዝጉጁ ነን” ተብሎ ለውጭ ዲፕሎማት ሲገለጽ መንግሥት ምን ያህል ግራ እንደተጋባ ጠቋሚ ነው። ከላይ ካስቀመጥናቸው ትንታኔዎች አንጻር የወያኔ/ህወሓት ብሎም የኦነግ ሸኔ ዛሬ ላይ የሀገራችንን እልውና መፈታተን የመንግሥት ድርሻ እንደተጠበቀ ዶር ዐብይ አሕመድ የሕዝባችንን የሀገር ፍቅር ተጠቅመው አሁንም ኢትዮጵያችንን ያድኑ ዘንድ ይህንን ዕድል የምንጠቁመው ሌላ አማራጭ ስለሌለን ነው። “ኢትዮጵያ አትፈርስም!” ሲባል አማራን ጨፍጭፎና አዳክሞ የምትገነባ ኢትዮጵያ አትኖርም። “ኢትዮጵያ አትፈርስም!” ሲባል ህወሓት በሀገር የመጣ ወንበዴ ቡድን መሆኑን የዛሬ 40 ዓመት የተረዳነው ቢሆንም በተጨማሪም ይህ መርዙ በተለይ በአንዳንድ ትግራይ ተወላጆች ላይ ሲንጸባረቅ ብናይም ኢትዮጵያችን ባዮች እንደነሱ መሆን አይገባንምና ህወሓትን ከትግራይ ሕዝብ ነጥለን መመልከት ይኖርብናል። ትግራይና የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያችን አካል ናቸውና ኢትዮጵያችን ስንል ትግራይን አቅፈን መሆኑን ለአፍታም መዘንጋት አይኖርብንም።

በተለያየ መልኩ ሀገራችን ላይ የሚከሰተው የታሪክ ድግምግሞሽ ትላንት አንድ ትውልድን በወጣትነት ብቻ ለመፍጀት በዱላ የተጀመረው አብዮት ጠባቂነት ወደ መሳሪያ ተለውጦና ለጠባቂዎቹ የማሰር፣ የመግረፍ፣ የመግደል መብት ሰጥቶ የተከሰተው ጥፋት ዛሬ በተከሰተው የህወሓት አሸባሪ ድርጊት በታወጀው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለነገ የሚተርፍ ቂም ቋጣሪ በቀል እንዳይሻገር ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ልንጠቁም እንወዳለን። የሰው ልጅ ሕግ ሊመለከታቸው የሚገባውን ጉዳይ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስም የማሰር መብት ሲሰጠው መስመር ሊስት ስለሚችል በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞች በስመ የትግራይ ተወላጅነት የሚደረግ ጥቃት እጅግ በጣም ጥንቃቄ ይደረግበት ዘንድ መጠቆም እንወዳለን። ወያኔ/ህወሓት ዘር ለይቶ ገዳይ ሆነና እኛም ይህንን ለማድረግ የደፈርን ዘንድ እውን ሀገር ተበጣጠሰች፤ የምናተርፈው ቂም የጨቋኝና ተጨቋኝ ወይም እፍኝ ከማይሞሉ ከአምባገነን ገዢዎች ጋር ሳይሆን አንዱ ዘር ከሌላው ይሆናልና ማን ላይ ማነጣጠር አለብን ስንል የኦሮሞ ኢትዮጵያውያንን ከኦነግ ነጥለን፣ “የተሳሳቱ” ትግራዮችን ከህወሓት ነጥለን መሆን ይኖርበታል።

የጠቅላይ ሚንስትር ዶር ዐብይ ኢትዮጵያ አትፈርስም ጩኸት አማራን እምሽክ አድርጎ፣ በተረኛ የኦሮሙማ ዘረኛ መንግሥት በተዋቀረ የሰለቸና ሀገርና ሕዝብ ያማረረ የዘር ፖለቲካ እንዲያበቃ

ካልተደረገ አሁን በተደረገው የክተት ዘመቻ ጦርነቱ አሸባሪው ህወሓትን በመቅበር ቢጠናቀቅ እንኳ ጊዜ እየጠበቀ እንደሚያገረሽ ውርዴ ተከታይ ትርምስ እንደሚኖር ያለማወላወል መግለጽ እንወዳለን። ***ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ መቀበር ያለበት ዘረኝነት ነው። ወደ ታሪክ ማህደር መከተት ያለበት የወያኔ ሕገ መንግሥት ነው። መናድ ያለበት ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገው አጥር ነው።*** የነገዋን ኢትዮጵያ እስከፊለግን ድረስ በዘር ሕገ መንግስት 30 ዓመት ሀገር ያጣችው ሀብት፣ የሰው ሕይወት ከበቂ በላይ ነው። ይህ ጦርነት የዛሬ 3 ዓመት ተኩል አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆ ሕገ መንግስቱን ለማፍረስ ክተት ተብሎ ቢሆን ሀገራችን እውን የለውጥ ጎዳናን በተሻገረች ነበር። ግና ያኔም እንዳልነው የወያኔ/ህወሓት ሕገ መንግሥት መጨረሻ አንቀጽ ሀገር ማፍረስ ነውና የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንገኛለን።

የአለፈው ምርጫን አስታኮ ጠቅላይ ሚንስትሩ መንግሥታቸውን ሲያዋቅሩ እና ቀጣይ መንግሥታቸው ሕገ መንግስቱን ተገን አድርጎ እንደሚቀጥል ቃለ መሃላ ሲያስደርጉ ህወሓት ቢቀበርም የቋመጡ ተረኛ የዘር ፖለቲከኞች በኦሮሙማ ስም ሀገር ዘረኝነትን ትሸከም ዘንድ የተደረገው ቅድመ ሹመትና ዝግጅት ሌላ የሀገራችን ጠንቅ መሆኑን እንጠቁማለን። ***ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያ እንድትቀጥል የሰሙኑ የሕዝብ መነሳሳት የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ መንግስትን ከመደገፍ አንጻር ሳይሆን ለሀገሩ አንድነት ያለውን ስሜት፣ ለሰንደቅ ዓላማው የሰጠውን ክብር ጠቋሚ ነውና መንግሥት ለራሱ ሲል ለመሠረታዊ ለውጥ ቢዘጋጅ እንመክራለን።*** በዘርም ከተመጣ ከእንግዲህ በምንም መልኩ አማራ እጁን ለዘረኞች አይሰጥም። ባለፉት የህወሓት መራሹ ኢሕአዴግ መንግሥትም ሆነ አሁን በአለው የብልጽግና አመራር ጊዜ በማንነቱና በሃይማኖቱ ጥቃት እየደረሰበት እየተፈናቀለና እየተፈጀ ያለው በተለይ “አማራ” ተብሎ የተሰየመው ሕዝብ ነው። በአብዛኛው “ኦሮሚያ”ና በሌሎችም ክልሎች በሚሊዮን የሚቆጠር የአማራ ሕዝብ የሚደርስበት መከራ አላባራም። ይህ ሕዝብ በሚኖርበት የአማራ ክልልም የትህነግና የአክራሪ ኦሮሞ ታጣቂዎች ጥቃት እያደረሱበት መሆኑ የየዕለት ዜና ነው። በመሆኑም እራሱን ከጥቃት የሚከላከልበት የታጠቀ ሕዝባዊ ጠባቂ ሊኖረው ይገባል። ይህን ደግሞ ከመንግሥት እንደ ገጸ በረከት ባይጠብቀውም እየተንቀሳቀሰ ያለው የአማራ ፋኖም ሆነ ልዩ ኃይል የተጠናከረ አመራር ገንብቶ ከአማራው እልውና ባሻገር በዘረኝነት መቃብር ላይ ኢትዮጵያችን እንድታሸንፍ ያለማወላወል ቆርጦ መነሳት ይኖርበታል። ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ አሸናፊዋ ኢትዮጵያ ድል የምትቀዳጀው የዘረኝነት መሠረቱን በመናድ ነውና የዚያ ጊዜ ወየው ለመንግሥት እንላለን። በወያኔ/ህወሓት ላይ የደረሰውና እየደረሰ ካለው ትምህርት መቅሰም ያልቻለ ዘረኝነት ከወያኔ መቃብር ሥር እንደሚወረወር የኢትዮጵያ ሕዝብ እያሳየ ነው። ጆሮ ያለው ይስማ፣ ዓይን ያለው ይመልከት፣ አፍ ያለው ይናገር ፈጣሪ ኢትዮጵያን የሚጠብቀው በዘር ለያይቶ ሳይሆን አንድ አድርጎ ነውና የአንድነቱ ጦርነት መደምደሚያው ዘረኝነት ቃሉ እንዳይነሳ አድርጎ የተቀበረ እለት ወየው ለሆዳሞች፣ ወየው አጠገባቹ ካለ ታሪክ መማር ለተሳናችሁ ከንቱዎች የናተም አቀባበር የከንቱ ከንቱ ይሆናልና ቆም ብላችሁ አስቡበት መልዕክታችን ይድረሳችሁ። ኢትዮጵያችን የአንድ ሕዝብ ሀገር፣ የበርካታ ብሔር/ብሔረሰቦች እናት ኢትዮጵያችን፣ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ዋልታ እናታችን ኢትዮጵያ ልጆቿን በኢትዮጵያዊነት የምታይበት፣ የምትሰበስብበት ጊዜው ትንሳዔዋ እንደተቃረበ ልንጠቁም እንወዳለን። ለዚህም ***ዛሬም ኢትዮጵያችን*** እንላለን።

*ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቅ!*
*ዘረኝነት ይውደም!*
*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!*
*አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን* ጥቅምት 28 ቀን 2014 ዓ.ም. (October 7, 2021)

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com ምሥለ ገጽ ፡ ፲ዘ፲ዘ Ethiopiachin